የቤተሰብ
የመረጃ ሉህ

# በሽታው መኖሩን የሚያረጋግጥ ውጤት፥
## የደም ምርመራ ውጤት ማሳወቂያ

የሚኔሶታ አዲስ የተወለዱ
ህጻናት ምርመራ ፕሮግራም

**Elevated TSH, Family Fact Sheet—Amharic**

# ከፍ ያለ ታይሮይድ አነቃቂ ሆርሞን (TSH, Thyroid Stimulating Hormone)

## አዲስ በተወለዱ ህጻናት ምርመራ የተገኘው ምን ነበር?

በወሊድ ወቅት የተወሰደው አዲስ የተወለደ ህጻን ምርመራ ልጅዎ ታይሮይድን የሚያነቃቃ ሆርሞን ተብሎ የሚጠራው ከፍተኛ የሆርሞን ደረጃዎች (TSH) ያለበት መሆኑን ያሳያል።

## ይህ ምን ማለት ነው?

ከፍተኛ የTSH ደረጃዎች ልጅዎ አብሮት የተወለደ የታይሮርይድ ሆርሞን እጥረት (CH) ያለበት መሆኑን ሊጠቁም ይችላል። CH የታይሮይድ በሽታ አይነት ነው። አብሮት የተወለደ ማለት ችግሩ የጀመረው በወሊድ ወቅት እና በአዋቂዎች ላይ ከሚታየው የታይሮይድ በሽታ የተለየ መሆኑን ነው። በበሽታው መያዝን የሚያሳይ የምርመራ ውጤት መቀበልዎ ልጅዎ የታይሮይድ በሽታ አለበት ማለት አይደለም፣ ነገር ግን በርግጠኝነት ለማወቅ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ቀጥሎ ምን ይሆናል?

የልጅዎ ሃኪም ተጨማሪ ምርመራ ያዛል። ልጅዎ በሚታከምበት ክሊኒክ ውስጥ ሁለት ቤተሙከራዎች ሊኖሩ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው። እነዚህ ሁለቱ ቤተሙከራዎች TSH እና ነጻ T4 (thyroxine) ተብለው ይጠራሉ።

በተጨማሪ በተደረገው ምርመራ የተገኘው ውጤት ጤናማነትን የሚያሳይ ከሆነ፣ ተጨማሪ ምርመራ ወይም ህክምና ማድረግ አያስፈልግም።

በድጋሚ በተደረገው ምርመራ የተገኘው ውጤት አሁንም ከፍ ያለ ከሆነ፣ የሚያስፈልገው ተጨማሪ ምርመራ ወይም ህክምና ምን እንደሆነ የልጅዎ ሃኪም ያሳውቅዎታል። የታይሮይድ በሽታ ያለባቸውን ህጻናት ወደሚያክም የህጻናት ኢንዶክሪኖሎጂስት ሊላኩ ይገባል።

## አብሮ የተወለደ የታይሮሮይድ ሆርሞን እጥረት (CH, congenital hypothyroidism) ምንድን ነው?

CH በአንገቱ የታችኛው ክፍል የሚገኘው አነስተኛ አካል የሆነው የህጻኑ ታይሮይድ እጢ ላይ እክል የሚፈጥር እና ህጻኑ ሲወለድ ጀምሮ ያለበት በሽታ ነው። ታይሮይድ እጢ የታይሮይድ ሆርሞን ያመነጫል። CH ያለባቸው ሰዎች በቂ የታይሮይድ ሆርሞን ማመንጨት አይችሉም። የታይሮይድ ሆርሞን ለጤናማ አካላዊ እና አእምሯዊ እድገት አስፈላጊ ነው።

## የሚያስከትላቸው የጤና ችግሮች ምን ምንድን ናቸው?

CH የእድሜ ልክ የጤና ችግር ነው። ካልታከመ የሚከተሉትን ሊያስከትል ይችላል፦

- የቆዳ ቀለም መወየብ (የቆዳ ቢጫ መሆን ወይም የአይን መንጣት)
- የጡንቻ ጥንካሬ ደካማ መሆን
- መማርን አስቸጋሪ ማድረግ
- የእድገት መዝገየት እና ከተገቢው በላይ መወፈር

CH ያለባቸው ህጻናት ከሚደረግላቸው አስቸኳይ እና ጥንቃቄ የተሞላበት ህክምና ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ያሉት የህክምና አማራጮች ምን ምንድን ናቸው?

ምንም እንኳን CH በህክምና መዳን ባይችልም፣ ሊታከም ይችላል። በጣም የተለመደው የCH ህክምና በትክክል እየመነጨ ያልሆነውን የታይሮይድ ሆርሞን የሚተካ መድሃኒት ነው። ምልክቶች ከመታየታቸው በፊት ከታከመ፣ ህጻናት ጤናማ አካላዊ እና አእምሯዊ እድገት ሲኖራቸው ይችላል።

CH ያለባቸው ህጻናት በመደበኛ ሃኪማቸው እና በታይሮይድ በሽታ ስፔሻላይዝ ባደረገ ሃኪም (ኢንዶክሪኖሎጂስት) መታየት አለባቸው።

## መርጃዎች

**የዘረመል መነሻ ማጣቀሻ፦**
http://ghr.nlm.nih.gov

**Save Babies Through Screening Foundation:**
www.savebabies.org

**የልጅ የመጀመሪያ ምርመራ፦**
www.babysfirsttest.org